# የኢትዮጵያ ምሁራንና የኢትዮጵያ ፪ሺ አከባበር

እስካሁን ያልሰሙ እንዳሉ፤ ኢትዮጵያውያን በያዝነው ዓመት መጨረሻ ላይ ሁለት ሺህ (፪፻፻) ዓመተ ምህረትን እንቀበላለን፤ እናከብራለንም። በተለይ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ድርጅቶች፤ የፖለቲካ ስብሰቦችና እንቅስቃሴዎች በሙሉ ከኢትዮጵያ መንግስት ነጻ በሆነ መልክ ይህንን ታላቅ በዓል ለማክበር በአንድነት መስራት፤ እንቅስቃሴያቸውንም ማቀናጀት ይጠበቅባቸዋል።

ይሁንና የኢትዮጵያ ፪፻፻ አከባበር ከሌሎች አገሮች በሰባት አመት ከተነጠለበት ምክንያት አንስቶ የአከባበሩን ዝርፎች፤ በታሪካችን፤ በስልጣኔያችንና በማንነታችን ላይ ያስከተላቸውንና ጥሎ የሚያልፋቸውን ቅርሶችና ችግሮች እንዲሁም ለመጭው ፳ ዘመን መቅሰም የሚገቡንን ትምህርቶች በአያሌው መመርመር፤ ለአከባበሩን አቅጣጫ መተለምና አመራር መስጠት የሚገባው ክፍል አለ። የምሁራኑ።

ምንም እንኳን ምሁር ወይም ምሁራን በሚለው ቃል ምንነት ላይ መስማማት አስቸጋሪ ቢሆንም በደራሲው አስተሳሰብ በሰፋት ተቀባይነት ያለውን ግርድፍ ፍቺ መጠቀም ለዚህ ጽሁፍ አላማ ያስኬዳል። ምሁር ሲባል «ሀሳቦችን በማፍለቅና በነሱው በመገልገል» የሚሰማራ ነው። ስለምሁራን ምንነት ቀደምትነት ያላቸው ጥናቶችን ባከናወነው የማሌሽያው ተወላጅ አላታስ አባባል «ምሁር» ማለት «ስለሀሳቦችና ቁሳዊነት ስለሌላቸው ችግሮች አእምሮውን ወይም ምክንያተኝነትን እየተጠቀመ የሚያስብ» ነው። ጨምሮም «የምሁራዊ እንቅስቃሴ ኢላማ ከህይወትና አስተሳሰብ ሰፊ ጀርባ ጋር ሁልጊዜ የተዛመደ መሰረታዊ እሴቶችንና እምነቶችን የመበርበር ነው።»

ባጭሩ «ምሁር» የሚለው ቃል በዘመናዊ ትምህርት ስርአት ገብተው በተለይ በዩኒቨርሰቲ ደረጃ ያስተሳሰባቸውን አቅም ያነጹ ወገኖችን ይመለከታል። በቀደምት የትምህርት ስርአቶች (ቤተ ክህነትና መስጊድ) ያለፉትን የማንጓጠጥ ጉዳይ ሆኖ እነሱን ከዚህ ፍቺ ማስወጣት የተለመደ ነው። ነገር ግን ከተሰጠው ግርድፍ ትርጉሙ አኳያ መለኪያው ያስተሳሰብ አቅምን የማነጽ ወይም ያለማነጽ እንጅ የገቡበት የትምህርት ተቋም መሆን አይገባውም። በሌላም በኩል ከዩኒቨርስቲ የተመረቀ ሁሉ ምሁር ለመባል አይችልም። በርግጥ ምሩቁ ሰው የቀሰማቸውን ሀሳቦች ይዞ በስራ አለም ስለተሰማራ ያስተሳሰብ አቅም አለው ሊባል ይችል ይሆናል። ሆኖም የግለሰቡ ስምሪት «ሀሳቦችን በማፍለቅና በነሱው መገልገል» ከሌለበት ምሁር ሊባል እንዴት ይችላል? ትምህርት ቤት በነበረበት ወቅት ያገኛቸውን እውቀቶች እየመነዘረ ለግል ኑሮው መሻሻያ ስላገኘ ብቻ የምሁርነት ካባ አያስጠልቀውም። ቢያንስ፤ አልታስን እንደገና በመዋስ፤ የራሱን የስልጣና መስመር ማበልጸግና ለሚከሰቱት ዝርዝር ችግሮች መፍትሄዎች ማፈላለግ ይጠበቅበታል።

ከላይ የቀረበው ፍቺ ባገራችን የሚገኙትን የተማሩ ወገኖች በተለይ ባልተጣራ ሚዛን ምሁር የሚሰኙትን ወይም ራሳቸውን ምሁር እያሉ የሚጠሩትን ሊያስደነግጥ ይችላል። በያጋጣሚው በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ውስጥ ይልቁንም እየገነነ በመጣው በኢንተርኔት ላይ አልፎ አልፎ «ዶክተር» እገሌ ብለው በሚጽፉት ሰዎች ላይ የሚሰነዘረው ዘለፋና «ከቴም ምሁር» የሚለው ግሳጼ መደጋገም ግን ምርቱን ከግርዱ የመለያው ወቅት መድረሱን ያበስራል። የዶክተሩ ብዛት ወይም የባለማስተሩ መርመስመስ (በውጭ አገሮች በተለይ በአሜሪካና በብሪትን) ላንዳንዶች ማለቂያ የሌለው ፌዝ ማጠንጠኛ ሆኗል። በአገራችን ላይ የተለያዩ ችግሮች ተደራርበው ባሉበት ወቅት እያደር ይበልጥ የሚሰማው የመፍትሄ ያለህ ጩኸት መሆኑ ምን ያህል ፌዙ ተጨባጭ መሰረት እንዳለው ያመለክታል። ቢያንስ ቢያንስ ችግሮቻችን ተራራ የማከላቸውን ያህል መፍትሄዎቻቸውም ካሉን ምሁራን አንደበትና ብእር እንደጎርፍ መፍሰስ ነበረበት። ማለትም ምሁራን በርግጥ ካሉን።

እንደውነቱ ከሆነ የኢትዮጵያ ትልቁ ችግር የሰከነም ባይባል የተሟላ የምሁር ክፍል አለመኖሩ ነው። ባለም አህጉሮች ሁሉ የተለያዩ ህዝቦችን ታሪክ በመቃኘት እንደምንረዳው ከግብርና ኢኮኖሚ ወደኢንዱስትሪ፤ ከፈላጭቆራጭ አስተዳደር ወደዲሞክራሲ፤ ከጎሳ ትርምስምስ ወደአንድ ወጥ ብሄራዊ ልእልና ላደረጉት ሽግግር የምሁራን አስተዋጽኦ የጎላ ነበር። በያገሮች ዝርዝር ታሪክ ውስጥ ልዩ ሁኔታዎችና ጠመዝማዛ የሽግግር ጎዳናዎች እንደነበሩ ቢታመንም የምሁራን አሻራ ያላረፈባቸው ምእራፎች ጥቂት ናቸው። ባለንበትም ዘመን ቢሆን እንደኢትዮጵያ ላሉ ያንን ሽግግር ላላከናወኑ በርካታ አገሮችና ህዝቦች የምሁራኑ ሚና በግልጽ የሚታይ ነው። ተሳትፏቸው ለፍሬ በቅቶ አገሮቻቸውን ወደፊት ለማራመድ ባይቻላቸውም በደማቸው የከፈሉት መስዋእትነት ቋሚ ምስክር ነው። ይህንን ከአፍርቃ እንኳን ከካሜሩን፤ አልጀሪያ፤ ሞሮኮ፤ ግብጽ፤ ኮንጎና ኢትዮጵያ የቅርብ ታሪክ መገንዘብ ይቻላል።

እዚህ ላይ በአውሮፓና በአሜሪካ የተከናወኑትን መለስ ብሎ መመልከትና ጠቃሚ ትምህርቶችን መቅሰም የሚዘገንናቸው ኢትዮጵያውያን እንዳሉ መጥቀስ ይገባል። ጊበን «ኢትዮጵያውያን በራቸውን ዘግተው፤ አለምን ረስተው በአለምም ተረስተው ለሺ አመታት ኖሩ» ያለውን ብቻ ተቀብለው በብቸኝነት የእንግፋ ሙግት አይነት። የመሳይ ከበደ «ከጥፋት መዳንና ዘመናዊነት፤የኢትዮጵያ እንቆቅልሻዊ ይዞታ» ይህን መሰል ጨኸት ያስተጋባል። ከዚያ በበለጠ ግን ትንሹንም ትልቁንም ያላንዳች ለውጥ ከነዚሁ አገሮች ለመቅዳት የሚሯሯጡ አሉ። ባገሪቱ የዩኒቨርስቲ ትምህርት (ኢኮኖሚክስ፤ ታሪክ፤ ምህንድስና ወዘተ) ያለፉ ከሞላ ጎደል የዚህ አቀንቃኝ ናቸው። ትንሽ ምሳሌ ለመጥቀስ ያገሪቱን የንግድና የኢንዱስትሪ አቅጣጫ በተመለከተ የረባ የኢኮኖሚክስ ጥናት የለም---ስማቸው ገናና ተበለው የተጠሩ ብዙ ኢኮኖሚስቶች ቢኖሩም!

ተወደደም ተጠላ ያለም ህዝቦች ላንድ ሺ አመታት ያህል በንግድ፤ በግዛት መስፋፋትና በቅኝ ገዥነት እርስበርስ ተሳስረዋል፤ ተተራምሰዋል፤ ተላልቀዋል። በመሃሉ በአሸናፊነት የወጡት ለተሸናፊዎች መተዳደሪያ ደንቦች ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ድርሻቸው ምን መሆን እንደሚገባው፤ የግንኙነታቸውን ባህርይ ወስነውላቸዋል። በመሆኑም ዛሬ አዲስ የተከሰተ አስመስለው አንዳንዶች የሚያወሩለት «አለምን የመጠቅለል እንቅስቃሴ» ስር ሲሰድ የቆየ መሆኑን ይገነዘቧል። ታዲያ የኢትዮጵያ ምሁራን ካለም ዳርቻ ቆመው አገራቸውንም ባህታዊ ሊያደርጉ ማሰባቸው ሆነ ባውሮጳና አሜሪካ ስም የተባሉትን አርቲቡርቲ ሁሉ ቀድተው ቢቸረችሩ ሁለቱም ላገርና ለወገን የሚፈይድ ትምህርት አያስተላልፉም።

በኢትዮጵያ ምሁራን መሀል እነዚህ አስተሳሰቦች መኖራቸው ሳያጠራጥር ምን ያህል ጉዳት እንዳስከተሉ መገምገሙ ግን ያስቸግራል። ላገራችን ውድቀትና ቁልቁል መውረድ የፖለቲካ ባለስልጣኖች በቀደምትነት የሚጠየቁ ቢሆንም ምሁራን ግን ቢያንስ ችግሮችን ለይተው በማውጣትና መፍትሄዎችን በመጠቆም በኩል የታየባቸው ከፍተኛ ጉድለት ከጥፋተኛነት አያድናቸውም። ይህን ለመረዳት በየዘርፉ የታዩትንና አሁንም የሚታዩትን ቅንጥብጣቢ መረጃዎች መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል።

በፖለቲካው መስክ በጣም የጎሉ ድክመቶችን በቀላሉ መጠቆም ይቻላል። ለምሳሌ ከሰሜን ብንጀምር የኤርትራ «ነጻ አውጭ» ገንባሮች ያልነበረ «ታሪክ» ፈጥረው «ሁሌም ነጻ ነበርን» የሚል ወሬ ሲያናፍሱ ከመሃላቸው ይህንን ቅጥፈት ለማጋለጥ የተነሱት አነስተኛ ናቸው። የኤርትራ ህዝብ የራሱ አካል ከሆነው ህዝብ ተቆርጦ ምን አይነት ነጻነት ሊኖረው እንደሚችል «ምሁር» በሚባሉት መካከል ጉዳዩ እንኳን ተለይቶ የታወቀ አልነበረም፤ ዛሬም እንቆቅልሽ እንደሆነ ነው። የሚገርመው ሻእቢያ መጀመሪያ የህወሀት የትግል አጋር ተብሎ በኋላም እንደጠላት ተፈርጆ በተመደበበት ወቅት ተቆርጦ የሚገነጠለው ወይም የሚወሰደው ህዝብ በምን መልክ እንደገና እንደሚዋሃድ ከሁለቱም በኩል በብዛት የሚነሳ ጉዳይ አይደለም። አንድ ወጥ የብሄር ነጻነት ወይም ልእለና

*ለማስገኘት ተጋድሎ ባደረጉት እንደጋሪባልዲና ማዚኒ በመሳሰሉት አይን ሲታይ ይህ ህዝብን እየሰነጣጠቁ «ነጻነት ተጎናጸፉ» የሚል አመለካከት ጎደሎ ብቻ ሳይሆን እንጭጭም ነው። ዞሮዞሮ ይህንን መሰረታዊ ጉዳይ ብቻ መመዘኛ ለማድረግ ብንቃጣ አንድ አቢይ ጥያቄ ላይ ይጥለናል፦ የኤርትራና ትግራይ ህዝብ ከቁጥር የሚገቡ ምንም ምሁራን አላደረሰም ማለት ነው?*

*በአማራው የተማረ ክፍል ውስጥ የኢትዮጵያን ታሪካዊ አመጣጥና ሂደት፣ የመንግስታቷን አወቃቀርና ባህርያት በተመለከተ ከተማሪዎች እንቅስቃሴና ከአብዮታዊ የፖለቲካ ድርጅቶች መወለድና እድገት ጋር ጭቆናዎችን በየገጽታው የመቃወምና አዲስ ምእራፍ የመክፈት ትልም ተቀዶ ነበር። ነገር ግን በተለይ በሶቭየት ህብረት እየተረዳ በህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ጫናውን የጣለው ደርግ ትልሙን አኮላሽቶት ከቦታው ተገፍትሮ ሲሄድ በምትኩ የተተካው የህወሀት መንግስት አገሪቱን በባሰ የተመሰቃቀለ ሁኔታ ላይ ጥሏታል። ካማራው ምሁራን መካከል በርካታው በደርግ ጭፍጨፋ ስላለቀና የበሰበሰውን ጥንታዊ ያገዛዝና የኢኮኖሚ ስርአት ለውጦ ዲሞክራሲን ተክሎ እድገትን ለማፋጠን የሚቀናጀው ሀይል በመቀነሱ የሽምቅ ተዋጊዎች ከትግራይና ከኤርትራ ድረስ ተጉዘው ባዲስ አበባው መንግስት ላይ ሲፈናጠጡ ዝር የሚል ወገን አልነበረም። ህወሀት በቂም የተመረዘ የስልጣንና የሀብት ሽግሽግ ላይ በማተኮር ብቻ ላገሪቱ መነሳትና ተሃድሶ ይሆኑ ዘንድ ተማሪዎችና አብዮታውያን ያራመዷቸውን መርሆዎች ረጋግጦ ጭራሽ ባልተጠበቀ ሁኔታ የጭቆናና የቀን ጅብ መንግስት መሰረተ። ጣልያን ካገራችን ከተባረረበት 1933 አመተ ምህረት ጀምሮ በፖለቲካ ትርምሶችና እንቅስቃሴዎች ሲናጥ የኖረው ህዝብ የደረሰበትን የንቃት ደረጃ ሊመጥን የሚችል ስራ መስራት ቀርቶ ህወሀት ዘመን የሻራቸውን የአመጽ አገዛዝና ተራ ዘርፊያ በመላ አገሪቱ ዘረጋ። በመሃሉም በጥሬው የሚያራግባቸው «የብሄሮች እኩልነት»ና «የመገንጠል ነጻነት» የህወሀት አመራር ቡድን ማጨበርበሪያ ሆነው ቁጭ አሉ።*

*የሚያስገርመው የህወሀትን ባዶ ስብከትና የጭቆና አገዛዝ ተቃውሞ የእኩልነት መገንቢያ መንገዶችን በማስተማርና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች መመሪያ እንዲሆኑ ከመገፋፋት ይልቅ በርከት ያሉ ያማራ ምሁራን ተብየዎች በታሪካችን ጭቆና እንደሌለብን ሽምጥጥ አድርገው በመካድ «ጸረ-ወያኔ» ሽፋን የያዘ ነገር ግን «ጸረ-ትግሬ» ዘመቻ ላይ ተፈናጠጡ። ትናንት ለኤርትራ መገንጠል የዳረጋት ዛሬም አገሪቱን ለርስበርስ መተናነቅ የሚገፋፈው አንዱ ምክንያት የብሄርና ብሄረሰቦች እኩልነት በተግባር አለመረጋገጥ መሆኑን  አሻፈረን አንቀበልም በማለት በሚፈጥሩት ልፈፋ «የኢትዮጵያን ኢምፓየር» ካላፈረሰን ብለው ለሚጋበዙት ስንቅ እያቀበሉ ከጀርባቸው ተሰልፈው ቆመዋል። በብሄርና ብሄረሰቦችረሰቦች ግንኙነት ውስጥ በተለይ በኢትዮጵያ መንግስት አወቃቀርና የስልጣን መጋራት በኩል መሰረታዊ ለውጥ መደረግ አለበት የሚሉትን ሁሉ «የጥፋት ሰራዊት» አድርገው በመሳል፣ ራሳቸውን ግን «የኢትዮጵያ አንድነት» ተማጋቾች አስመስለው ሲቀባጥሩ አገሪቱን እያደር ወደሚገር ቀውስ ገፋፍተዋታል። የጭፍንነታቸው ብዛት የወያኔ መሪዎችን ያገዛዝ ጥፋቶችና ወንጀሎች በተራው አባላትና በትግራይ ህዝብ ከማላከክም አይመለሱ።*

*በቀርቡ በቅንጅትና በኦሮሞ ነጻአውጭ ግንባር እንዲሁም ሶስት ሌሎች ድርጅቶች መሃል የተፈጠረውን ፖለቲካዊ የመደጋገፍ ስምምነት አስመልከቶ ባንዳንድ ክፍሎች የተነዛው ውዥንብር የዚያው ቢጤ ነው። ባንድ በኩል ለፖለቲካ መደጋገፍ ሙሉ ያስተሳሰብ መመሳሰል መኖር እንደሚገባው ያህል ይዘብቱና በኦነግና በቅንጅት መሃል ከቶ እንዴት መተባበር ሊኖር ይችላል? ብለው ይሞግታሉ። ኦነግ አስቀድሞ «ኢትዮጵያዊነቱን» ተቀብሎ ያንድነትን አላማ ካላራገበ «የቅንጅት አለማቀፍ አመራር» «ትብብር» ብለው መፈረማቸው በፕሮግራማቸው ላይ ያሰፈሩትን መካዳቸው ነው ይላሉ። በሌላ በኩልም ከየድርጅቶቹ ጀርባ የቆሙ «ጸረ-ኢትዮጵያ» ሃይሎች ስላሉ ቅንጅት በፖለቲካዊ የመደጋገፍ ስምምነት ውስጥ በመግባቱ ራሱን ለጠላት መሳሪያ አድርጓል ብለው ይጮሃሉ። በዚያም ሆነ በዚህ ዱሮም አልነበረም ዛሬም የለም ብለው ለሚሸመጥጡት*

የብሄርና ብሄረሰቦችረሰቦች መበላለጥ ወይም ጭቆና መፍትሄ ማስገኛ መንገድ እንዳይከፈት ይፍጨረጭራሉ። በትብብሩ መመስረት በአዲስ አበባው መንግስት በኩል የተፈጠረው መደናገጥና መርበትበት እንኳን ሀሳባቸውን የሚያስለውጥ የተለየ ምልክት አልሆነላቸውም። በፖለቲካ ቲወሪም ሆነ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ያልተደገፈ ጭፍን ያንድነትና ወጥ የፖለቲካ ህብረት እየቀባጠሩ ያገሪቱን ችግሮች ከዘመን ዘመን እንዲሸጋገሩ ያግዛሉ።

ከኦሮሞ ምሁራን መሀል እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ከሚለው ስም አንስቶ ኦሮሞ ያልሆነውን ህዝብ ጨምሮ በምድር ገጽ ላይ እንደሌሉ የመቁጠርና የተናጠል ትግልና ኑሮ የመያዝ ምስጢር ፍቺ ምን እንደሆነ አይታወቅም ነበር። «ኢትዮጵያ» ማለት ማንም ወደደ ጠላ ባለም አቀፍ ግንኙነቶች ውስጥ ታሪካዊ ስፍራ ያላት፣ በመንግስታት ስብጥር ውስጥ እውቅና አግኝታ ለእልፍ ዘመናት የኖረች ግዙፍ አካል መሆኗን ክደው «ምስራቅ አፍሪቃ»፣ «ያፍሪቃ ቀንድ» ወዘተ በሚሉ ተክተው በቅዠት ዳመና ውስጥ ሲዋኙ ኖረዋል። በፖለቲካ ሀሁ ውስጥ የነበረንና ያለን በፈጠጠው አይን ተመልክቶ በአእምሮ ማረጋገጥ የሚገባ ሲሆን በተጠቀሱት የኦሮሞ ምሁራን በኩል ግን የህልም ቧጠጣ መሳሪያቸውና መናጃቸው ሆኖ ኖሯል። አማርኛ መናገር እንደሀጢያት፣ በሳባዊ ፊደሎች መገልገል እንደመዋረድ (ባንጻሩም በላቲን መጻፍ የነጻነት ብሎም ለሳይንስና ለጥበብ የመዘጋጀት ምልክት) አድርገው በማቅረብ፣ ባገሪቱ ህዝባዊ ድርጅቶች (የሰራተኞች፣ የመምህራን፣ የተማሪዎች) ውስጥ በየብሄር መኮልኮለን እንደዘዴ በማራመድ በሁሉም መልክ የተገነጠለች ኦሮምያን በጃቸው ያስገቡ በማስመሰል ሲያራግቡ ለኦሮሞ ህዝብ ቅጥ አምባሩ የጠፋበት ውዥንብር ነዝተዋል። ውዥንብር በየትኛውም የፖለቲካ ሰልፍ ላለ ድርጅት በተለይ ለፈረደበት ህዝብ የሚያስከትለው መውጫ የማይገኝበት ትርምስምሰና የማያልቅ ሰቆቃ መሆኑ ገና ሙሉ ለሙሉ አልተሰማቸውም። ሀያ ሺህ ጦር አሰልፈው ወደህወሀት እስር ቤት እንዲወረወሩ ያስቻለው ይኸው ውዥንብር ነበር። በውዥንብሩ የታጀበው የፖለቲካ እሽክርክሪት ማለቂያ የሌለው መሆኑ ሲታይ ከሌሎች ጋር አብሮ ጎንበስ ቀና ማለት በቅርቡ ቢጀመርም «የዘዴ» ለውጥ እንጅ የእውቀት መጨበጥ ውጤት አይመስልም። እንኳን የሚመለከቷቸውን ዋናዋና የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጉዳዮች መርምረው መልስ ሊሰጡና የትግላቸውን አቅጣጫ ሊቀይሱ በርካታ ሰዎች በተደጋጋሚ ላቀረቡት አነስተኛ ትችትም የሚጥም ሀተታ አላቀረቡም። (የኦሮሞ ህዝብ እንደሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፈላጭቆራጭ አገዛዝ ለመውጣትና ዘርፈ-ብዙ ችግሮቹን አሸንፎ በሰላም ለመኖር መታገሉ የማይገሰስ መብቱ መሆኑን ልብ ይሏል።)

ከዚህ በላይ ለምሳሌነት የጠቀስናቸው በፖለቲካው ዘርፍ ከየምሁራኑ በኩል የሚታዩትን ዋናዋና ግድፈቶች ነው። ዘርፉ ዝርዝር ትንታኔና ጥናት የሚጠይቅ ስለሆነ ባጭሩ መቅረቡ የቅምሻ ያህል ወርውረን ጨረስን ለማለት አይደለም። ጊዜና አቅም ያላቸው በስፋት ቢመለከቱት እንደሚበጅ አያከራክርም። ይልቅስ ሌሎች ተመሳሳይ ግድፈቶች የሚታዩባቸውን ዘርፎች ለመጥቀስ እንሞክር። የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክና የቅርሳቅርሶቿን ምንነት፣ የመንግስታቷን አመሰራረትና አወዳደቅ፣ የተለያዩ ባህሎችና ህዝባዊ ፍልሰቶች እንዴት ተቀናጅተው የዛሬዋን አገር ከተለያዩ ቋንቋዎችና እሴቶች ጋር ትተው እንዳለፉ የውጭ ባለጥቅም ጸሀፊዎችና ተመራማሪዎች ከሚተርኩት ውጭ በኛ ምሁራን አንደበት የተከናወነው እዚህ ግባ የማይባል ነው ወይም ብዛት የሚታወቅ አይደለም። ዛሬ ተደቅኖብን ላለው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሽግግር ተጋድሎ በታሪካችን ውስጥ ሲፈተሉ የቆዩትን ገመዶች ለመጨበጠና በወጉ እንዳስፈላጊነቱ አርግቦ ወይም አጥብቆ ለማሰር ወደኋላ መሰል ብሎ መቃኘትን ይጠይቃል። አሊያ እንደነባክስተርና ገሪንፊልድ የመሳሰሉት የነዙትን ማንዘራሽ የታሪክ አሜከላዎች በመመንዘር ከጥፋት ወደጥፋት መውረድ ይቀጥላል።

እንደገና አንድ ምሳሌ እንድናቀርብ ይፈቀድልን? ዛሬ የኢትዮጵያ መሀል አገር ተብሎ የሚጠረው ወሎና ሰሜን ሸዋ ላይ የሚኖረው ህዝብ በአክሱም ዘመንና ከዚያ በፊት ምን

ቁንቋና አስተዳደር ነበረው? በኋላስ ምን ደረሰ? በተለምዶ የሚተረከውን ከሰማን ካክሱም መፍረስ በኋላ ገናና የነበረው ያገው መንግሰት (ከነቃሉ «የዛጌ» መንግስት) ነው። ከዚያ እስካሁን ድረስ ስሟ በትክክል የልተገለጸው «ዮዲት ጉዲት» ስልጣን ጨበጠች። እሷ ከተሸነፈች በኋላስ የህዝቡ ሁኔታ ምን በቃው? ለ500 አመት ያህል የተደረገውን ትርምስ ያጠቃለለ እውቀት ከየት እናግኝ? በተለይ ለትግርኛና አማርኛ ቋንቋዎች በተከታታይ (??) መወለድ ምክንያቶቹና ሂደቶቹ ምንድር ናቸው? ሌሎችም በርካታ ጥያቁዎች መልስ ይሻሉ። እነዚሁ ጥያቄዎች በደቡብ ላለው ህዝብም በተለይ ለሲዳማ (በሰፊው አባባል)ና ሀዲያ ህዝቦች መቅረብ የሚገባቸው ናቸው።

የኢትዮጵያውያን ምሁራን ግድፈቶች የመብዛታቸውን ያህል በተለይ በያዝነው አመት እላይ እንደተባለው የ፪፻ ዘመንን ለመቀበልና ለማክበር ስለታደልን ወቅቱን ተደግፈን ብዙ መስራት እንችላለን። የምሁራን ልዩ ተግባራት ያገራችንን ታሪክ፣ ቅርሳቅርሶች፣ ባህል፣ ጥበባትና አስተዳደር ወደኋላ መለስ ብሎ ለማስተዋል፣ ለማጥናትና ለመመርመር ብሎም ለ21ኛው መቶ ዓመት የሚያገለግሉንን ትምህርቶች ለመቅሰም የሚያስችሉ በርካታ ዐውደ-ጥናቶችና ስብሰባዎች ማካሄድ ይመስለናል። ዓመቱ እስኪገባደድ ድረስ በዓሉ የኛው በመሆኑ በዐውደ-ጥናቶች በስብሰባዎችን በድግሶች ላይ እየተጋበዙ ዕውቀቶቻቸውን የሚያካፍሉን ኢትዮጵያውያን ምሁራን ብቻ መሆን ይገባቸዋል። የውጭ አገር አዋቂዎችና ተመራማሪዎች ምንም ያህል ለኢትዮጵያ ወገናዊነት ቢኖራቸውም የድግሱ ተካፋይ እንጅ ደጋሽ ሊሆኑ ከቶ አይገባም። ይህም አላማ እንዲሳካ የሚመለከታችሁ ወገኖቻችን ሁሉ በትጋት መሳተፍ ይኖርባቸዋል። ተመልሶ በማይመጣ በዚህ ታላቅ ወቅት ሰበብ የራሳችንን የታሪክ ጉዞ እራሳችን መርምረን ለራሳችን ሰብእናና ማንነት ዋልታ ማድረግ ካልቻልን ማንን መልሰን እንከሳለን?

ፈረሱም ይኸው ሜዳውም ይኸው እንዲሉ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ማንነታቸውን የማስመስከሪያ ወይም መቅበሪያ ፈተና እነኾ ከፊታቸው ተደቅኗል።

አሰፋ እንደሻው
ለንደን፣ ኢንግላንድ
ታህሳስ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ አም